መልእክት ስድስት

**የመጽሐፈ መሣፍንት ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም**
**እና**
**ለእግዚአብሔር በነበራት አምልኮ የእስራኤል ክህደት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ መሣ. 1፡1፤ 2፡1፤ 17፡1-5፤ 18፡1፣30-31፤
2 ተሰ. 2፡2-3፤ 2 ጴጥ. 1፡3-21፤ 2፡1፣ 15

**I. የመጽሐፈ መሣፍንትን ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ማወቅ ያስፈልገናል፦**

ሀ. በመሣፍንት 1፡1-20 የእስራኤል እግዚአብሔርን መፈለግ የእስራኤልን በእግዚአብሔር ላይ መታመን ውብ ትዕይንት ይገልጻል፤ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ሕይወታዊ ጥምረት እንደ ምሳሌ አስቀድሞ በማሳየት ከጌታ ጋር ያለ አንድነትን የሚያሳየው ይህ ድንቅ ስዕል በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ 6 የተገለጸው የእስራኤል ሕዝብ መጀመሪያ ወደ መልካሚቱ ምድር ሲገባ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የነበረው አንድነት መቀጠል ነው—ዘኁ. 27፡21፤ 1 ሳሙ. 22፡10፤ 23፡9-10፤ 2 ሳሙ. 2፡1።

ለ. በብሉይ ኪዳን ሙሉ ስፋት መሠረት በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ ሚስት አገባ—ዘጸ. 20፡6፣ የግርጌ ማስታወሻ 2፦

1. እግዚአብሔር በጽንሰ-ሃሳቡ እና በመሻቱ መሠረት የእስራኤል ባል ለመሆን ፈልጎ ነበር፣ በዚህ ድንቅ የትዳር ጥምረት ውስጥ ከእርሱ ጋር ባለ እጅጉን የፍቅርና የቅርብ በሆነ ግንኙነት እስራኤል ደግሞ የእርሱ ሚስት እንድትሆን ፈልጎ ነበር።
2. ሳሙኤል የታሪክ መጽሐፍትን ሲጽፍ እስራኤል ከባሏ አኳያ የኖረችውን ኑሮ ለእኛ ለማሳየት በቅደም ተከተል መጽሐፈ መሣፍንትን ከመጽሐፈ ኢያሱ በኋላ አስቀምጦት ነበር።
3. በመጽሐፈ መሣፍንት እንደተገለጠው እስራኤል የያሕዌ ሚስት ለመሆን ልቡ አልነበራትም፤ ይልቁንም እንደባሏ እግዚአብሔርን ተወችው፣ እንደ ጋለሞታም ሌሎችን አማልክት ለመፈለግ እና እነርሱን ለማምለክ ተንቀሳቀሰች—2፡11-13፣ 17፤ 3፡7፤ 8፡33፤ 10፡6፤ ተዛ. ኤር. 11፡13፤ ሕዝ. 16፡25-26፤ ሆሴ. 1፡2፤ 2፡2።

ሐ. በመሣፍንት 1፡1-20 ካለው ከይሁዳ እና ከካሌብ ታሪክ በኋላ በዚህ መጽሐፍ የተዘገበው የእስራኤል ታሪክ በአንድ ጋለሞታ መበስበስ እና መበላሸት የተሞላ ነው፦

1. የኢያሱ መጽሐፍ እስራኤል በከነዓን ነዋሪዎች ላይ በተቀዳጀችው ድንቅ ድሎች የተሞላ ሲሆን፣ መሣፍንት ግን እስራኤል ያሕዌን በመተዋ ከጠላቶቿ በደረሰባት አሳዛኝ ሽንፈቶች የተሞላ መጽሐፍ ነው።
2. ይህ የመሣፍንት ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ነው።

መ. የመሣፍንት ይዘት የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ላይ መታመናቸውን፣ እግዚአብሔርን መተዋቸውን፣ በጠላቶቻቸው መሸነፋቸውን፣ በአሳዛኝ ሁኔታቸው ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ መግባታቸውን፣ በመሣፍንቱ አማካኝነት ነጻ መውጣታቸውን እና እንደገና ደግሞ መበላሸታቸውን ያካትታል፤ ይህ በመሣፍንት ሰባት ጊዜ የተደገመ አዙሪት ነበር—1፡1-2፤ 2፡11—3፡11።

**II. መሣፍንት 2፡1 ስለ ያሕዌ መልአክ ይናገራል—5፡23፤ ዘኁ. 22፡22፦**

ሀ. እንደ ባሪያ የእግዚአብሔርን ምርጦች በማገልገል፣ የያሕዌ መልአክ በመለኮታዊው ሥላሴው እግዚአብሔር ራሱ ነው—ተዛ. ዕብ. 1፡14።

ለ. የሥስታንዱ አምላክ አካል መልበስ ክርስቶስ ነው፣ እና ክርስቶስ ደግሞ በብሉይ ኪዳን እንደ ያሕዌ በድርጊት እስራኤልን የተንከባከበ የያሕዌ መልአክ ነው—ዘጸ. 3፡2፣ የግርጌ ማስታወሻ 1።

ሐ. ክርስቶስ የያሕዌ መልአክ መሆኑ ትርጉሙ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመንከባከብ በመለኮታዊው ሥላሴ ራሱን መሾሙ እና ተልዕኮ ለራሱ መስጠቱን ነው።

መ. እስራኤል እንደ ተገቢ ሚስት ስላልተንቀሳቀሰች የእስራኤል ባል፣ ራስ እና ንጉሥ የነበረው እግዚአብሔር ራሱ ለሚስቱ አገልጋይ ሆነ፦

1. ያሕዌ ወደ እርሷ የመጣው እንደ ባል፣ እንደ ራስ ወይም እንደ ንጉሥ ሳይሆን በያሕዌ እንደተላከ እንደ የያሕዌ መልአክ ነበር—ዘካ. 2፡9-11።

2. እስራኤል ያሕዌን እንደ ራስ እውቅና ስላልሰጠችው እርሷን ለማገልገል ባርያ ሆነ፤ በመሣፍንት 2፡1-3 ለእስራኤል የሰጠው ቃል ተግሣጽ ወይም ትእዛዝ ሳይሆን የባርያ ምክር ነበር።

## III. ለእግዚአብሔር በነበራት አምልኮ የእስራኤልን ክህደት መሣፍንት 17 እና 18 ይገልጣሉ፡-

ሀ. ክህደት ማለት የእግዚአብሔርን መንገድ መተው እና ከእግዚአብሔር ውጭ የሆኑ ነገሮችን ለመከተል ሌላ መንገድ መውሰድ ነው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እና እግዚአብሔርን በማምለክ ካባ ለራስ ነገሮችን ማድረግ ነው—ሐዋ. 9፡2፤ 18፡26፤ 2 ጴጥ. 2፡2፣ 15፣ 21፤ ይሁ. 11፤ መሣ. 18፡30-31።

ለ. "ሰውዮውም ሚካ የአምላክ ቤት ነበረው፤ ኤፉድና ተራፊም አደረገ፥ ከልጆቹም አንዱን ቀደሰው፥ ካህንም ሆነለት"—17፡5፡-

1. እንደ የአማልክት ቤት የሚካ ቤት፣ ከጣዖቶቹ ጋር (እንደ የክርስቶስ ምትኮች)፣ ኤፉዱ (የእግዚአብሔርን ሥልጣን በመወከል)፣ እና የተቀጠረው ካህን (የአገልጋይ-ተገልጋይ ሥርዓት በመወከል፣ ቁ. 7-13) እግዚአብሔርን ማምለክ በተመለከተ ዛሬ በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ክህደት ያሳያል።
2. የሚካ እናት ለእግዚአብሔር የሆነ መሥዋዕት አቀረበች፣ መሥዋዕቷ ግን ከጣዖት አምልኮ እርሾ ጋር የተቀላቀለ ነበር (ቁ. 1-4)፤ የዚህ አይነት የቅልቅል እና የክህደት ሁኔታ በክርስትና ውስጥ አለ።
3. የሚካን "የአማልክት ቤት" (ቁ. 5) ስዕል በክርስትና ሁኔታ ላይ መተግበር እንችላለን።
4. የዛሬው ክርስትና ብዙ "የሚካ ቤቶች" አሉት፤ የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ የመንግሥት አብያተ ክርስቲያናት፣ ዲኖሚኔሽኖች፣ እና ብዙ ኢ-ጥገኛ የሆኑ ቡድኖች ክርስቶስን በሚተኩ በብዙ ጣዖታት የተሞሉ "የሚካ ቤቶች" ናቸው።

ሐ. "የዳንም ልጆች የተቀረጸውን ምስል ለራሳቸው አቆሙ፤" እና "ሚካም ያደረገውን የተቀረጸ ምስል የእግዚአብሔር ቤት በሴሎ ባለበት ዘመን ሁሉ አቆሙ"—18፡30-31፡-

1. የዳን ክህደት ከፋፋይ የአምልኮ ማዕከል መመሥረቱ ነበር—17፡9-10፤ 18፡27-31፤ 1 ነገ. 12፡26-31።
2. ዳን እንደ የአንበሳ ደቦል ብዙ ምድር ለማግኘት ታገለ (ክርስቶስን በማመልከት)፣ ነገር ግን ስኬታማ ከሆነና ድልን ከተቀዳጀ በኋላ ታበየ፣ ግለሰባዊ፣ እና ኢ-ጥገኛ ሆነ—ዘዳ. 33፡22፤ ኢያ. 19፡47፤ መሣ. 18፡27-31።
3. የዳን ወገኖች ያገኙት ነገር ትዕቢተኞች እና ኢ-ጥገኛ፣ እና ለጌታ ድንጋጌ ለመገዛት ፈቃደኛ እንዳይሆኑ አደረጋቸው—ቁ. 1-31፤ ዘዳ. 12፡5፣ 8፡-
   ሀ. ዳን ስኬታማ ስለነበር ትዕቢተኛ እና ግለሰባዊ ሆነ፤ ለራሱ እንጂ ለሌሎች ግድ የማይሰኝ ሆነ—33፡22፤ መሣ. 18፡27-31።
   ለ. የዳን ክህደት ምንጭ ለሌሎች ነገዶች ግድ አለመሰኘቱ ነበር፤ ለአካሉ ሌሎች ክፍሎች ግድ አለመሰኘት የክህደት ምንጭ ነው።
4. በመላው የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከዳን ከፋፋይ የአምልኮ ማዕከል መመሥረት ክህደት በላይ ኃጢአት የተሞላ ወይም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉዳት ያደረሰ ሌላ ክስተት አልነበረም—ዘፍ. 49፡16-18፤ ዘዳ. 33፡22፤ መሣ. 18፡1፣ 30-31።
5. እያንዳንዱ ከፋፋይ ማዕከል ለሆነ ግለሰብ የግል ፍላጎት የተቋቋመ ነው፤ እንዲህ አይነት ልምምድ ክፍፍል ብቻ ሳይሆን ውድድርንም ጭምር ያመጣል—ቁ. 1፣ 13-31፤ ዘፍ. 49፡16-18፤ ዘዳ. 33፡22፡-
   ሀ. የመገናኛው ድንኳን በሴሎ ውስጥ ነበር፣ የተቀረጸው ምስል ደግሞ በዳን ውስጥ ነበር—ኢያ. 18፡1።
   ለ. "...የተቀረጸ ምስል የእግዚአብሔር ቤት በሴሎ ባለበት ዘመን ሁሉ አቆሙ"—መሣ. 18፡31፤ 1 ሳሙ. 1፡3።
6. በክርስትና ታሪክ ውስጥ ለሌሎች ለመገዛት ፈቃደኞች ያልነበሩ፣ ነገር ግን ሌላ የአምልኮ ማዕከል የመሠረቱ ብዙ "ዳኖች" ነበሩ—መሣ. 18፡1፣ 13-31።
7. ወደ ክህደት ውስጥ ከመውደቅ ምርጡ የመጠበቂያ መንገድ ለመላው አካሉ እና በአንዱ የጌታ ሥራ ውስጥ ለጌታ ልዩና ብቸኛ ምስክር በመጠንቀቅ ነው—1 ቆሮ. 10፡17፤ 12፡12፣ 27።

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ ከመመለሱ በፊት ታላቅ ክህደት በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እንደሚኖር ጠንካራ ትንቢት አለ—2 ተሰ. 2፡3፡-

1. አስቀድሞ ክህደቱ ሳይመጣ የጌታ መምጫው ቀን አይመጣም—ቁ. 2-3።
2. በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠው ይህ ክህደት ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ቀጥተኛው መንገድ መውደቅ ይሆናል—1 ጢሞ. 1፡4፤ ኤፌ. 1፡10፤ 3፡9።

3. ዛሬም ቢሆን በአንዳንድ ክርስቲያኖች መካከል የአዲስ ኪዳንን ቀጥተኛ መንገድ የመተው ዝንባሌ አለ—2 ጴጥ. 2፡15።

ሠ. የ 2ኛ ጴጥሮስ ቅድመ ሁኔታ እና ሸክም ክህደት—ከእግዚአብሔር እውነት ትክክለኛው መንገድ መውጣት—ነው—2፡1፦

1. ክህደቱ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ፣ እንቆቅልሽ ወደ ተሞሉ የሰው አመክኗዊ አስተሳሰቦች አማኞችን በመምራት ትኩረታቸውን ከፋፈለ—ቆላ. 2፡8።
2. የከሃዲያን ትምሕርት አማኞችን የሕይወትን ዛፍ ወደመካፈል ሳይሆን ሞት ወደሚያመጣው የእውቀትን ዛፍ ወደ መካፈል መራቸው—ዘፍ. 2፡9፣ 16-17፤ 2 ቆሮ. 11፡2-3፣ 12-15።
3. ክህደትን ለማስወገድ ጴጥሮስ የተጠቀመባቸው ጸረ-ክህደቶች የሕይወት እና የእውነት መገለጥ አቅርቦቶች ነበሩ—2 ጴጥ. 1፡3-21፦
   ሀ. በቁጥር 3 እስከ 11 ጴጥሮስ ተገቢ ለሆነ የክርስቲያን ሕይወት የመለኮታዊውን ሕይወት አቅርቦት እንደ ጸረ-ክህደት ክትባት ተጠቀመ።
   ለ. በቁጥር 12 እስከ 21 ጴጥሮስ በክህደት ያለውን ኑፋቄ ለመጻረር የመለኮታዊውን እውነት መገለጥ እንደ ክትባት ተጠቀመ—2፡1፣ የግርጌ ማስታወሻ 3።
4. የዛሬው ክርስትና በክህደት የተሞላ ስለሆነ ጌታ ምለሳ ያስፈልገዋል—የሕይወት እና የእውነት ምለሳ—ዮሐ. 1፡4፤ 8፡12፤ 10፡10፤ 14፡6፤ ራእ. 2፡4፣ 15።

ረ. ዛሬ፣ በክህደት ዘመን፣ የንጹሑን ቃል ሙሉ መገለጥ መመስከር እና በእግዚአብሔር ቃል ለተገለጡት ጥልቅ እውነቶች መዋጋት ያስፈልገናል፣ ይህ ደግሞ የሚከተሉትን ያካትታል፦

1. የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ የሚመለከተው መገለጥ—ኤፌ. 1፡10፤ 3፡9።
2. መለኮታዊውን ሥላሴ የሚመለከተው መገለጥ—2 ቆሮ. 13፡14፤ ራእ. 1፡4-5።
3. ሁሉን-ያካተተውን የክርስቶስን ማንነት እና ሥራ የሚመለከተው መገለጥ—ቆላ. 2፡9፣ 16-17፤ 3፡11።
4. የተጠናቀቀውን ሕይወት-የሚሰጠውን መንፈስ የሚመለከተው መገለጥ—ዮሐ. 7፡39፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ራእ. 22፡17።
5. የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ሕይወት የሚመለከተው መገለጥ—ዮሐ. 3፡15-16።
6. የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የሆነችውን የክርስቶስን አካል የሚመለከተው መገለጥ—ኤፌ. 1፡22-23፤ 1 ቆሮ. 12፡12-13፣ 27፤ 10፡32።

*© 2021 Living Stream Ministry*